# ነጥልና ዘርር

በኮስሞስ-2000, February 2010



ደመ መራራ ነው	አንዳንዱ ሰውማ
ባልዋለበት ድርጊት	ሁልጊዜ እየታማ
ኀጥያተኛነቱን	ደጋግሞ እየሰማ
ኑሮይቱን ይኖራል	ኑሮ ካሉትማ::
አገር ሙሉ በደል	በሥፍር ተሠፍሮ
ሲጭኑት ከላዩ	አንገቱ አቀርቅሮ
መቋቋም አቅቶት	በዝቶበት እሮሮ
ብሶቱን ጭንቀቱን	ለፈጣሪው ነግሮ
ዕውነትም የለህም!	ብትኖርማ ኖሮ!
ወርደህ ትፈርድ ነበር	ሳትሰጥ ቀጠሮ
ብሎ ይተክዛል	አንዱየን አማርሮ::

አንጀቱ እያረረ	ግን እያሳየ ፈገግታ
ዘፈን ከመረጠም	ለሳቅ ለጨዋታ
ተው ቻለው ሆዴ ነው	የሚሰጠው እርካታ::
መምሰል እንዲህ ቀላል	ባትሆንም ላንዳንዱ
አበጀ! ጎበዝ!	መስሎ አዳሪ ነው እርሱ!
ሆኖ ቁም ነገሩ	ዘመናዊ ልምዱ
ባህል ስለሚሆን	በዚህ ከነጎዱ
ባይዋጥለትም	የተያዘው ወጉ
አብሮ እየደነከረ	እያሳየ ውሸክታ

ከባለ ጊዜ ጋር ይመታል እስክስታ::

ቆዳው ሞኝ መሳይ ውስጡ ተንኮለኛ
በሴራ እያጠቃ ሲኖር ሞገደኛ
እየተበራከተ የሃገር ቀበኛ
ለዓይነት እንኳን ያህል ሲጠፋ ሃቀኛ
ልቡ እንዲህ ሲሰበር ሆነ አዘንተኛ::
ኀዘኑ ትካዜው አይደለም ለግሉ
የሚመጣው ትውልድ ሳይደላደሉ
ሽክፍክፍ ሳይሉ
ዓይናቸው እያየ በቁም እንዳይበሉ::
እራሱ ጨፍጭፎ እራሱ አበላሽቶ
ሰይጣናዊ ግብሩ እንዳይወጣ ጎልቶ
ሌላውን ያሳጣል ፍጥር አርጎ ዋሽቶ::
የእኔ ቢጤው የዋህ
ምንም ሳያስበው ሆኖ ተጠርጣሪ
እንዲያም ሲል ይሆናል በግረ-ሙቅ ታሳሪ::
ሕግ አውጭ እየሆኑ ዳኛና መስካሪ
ሃቀኞች ተጠቁ በነገረ ሠሪ::
ለተደበደቡት ለተነቀሉቱ
ብቻ ቤት ይቁጠረው በየመጡበቱ
ታሪካቸውን ፃፉ አንዷንም ሳትስቱ::

ሃቅ አፈግፍጋ ግፍ ቢደርሳት ተራ
የበደለኞቹ ገበያቸው እየደራ
እየተደጋገፉ
ሕግ ሳይገዛቸው እየመዘበሩ

እንዳይጋለጡ
ዐዋቂዎቻችን    አባረው ካገሩ
ጀግኖቻችን ለቀው    አገርን ወረሩ::
እንደዚህ ከሆነ    የሰው ዕጣ ዕድሉ
ተንኮፍኮፍ እያረጉ    ከሥሩ ሳይነቅሉ
ተመልሰው ሊያድጉ    ያጨበጭባሉ::
ዛሬን ያልሠሩባት    ያላስተካከሉ
ሕዝብን አደራጅተው    ዛሬ ያልታገሉ
እርባና አይኖረውም    ኋላ ወይኔ ቢሉ::

በእንስሳ አስመስዬ    በደሌን ላሳውቅ
ስም ላወጣ ብዬ    ስሜት ላንጸባርቅ
ውሻ አሳድጋለሁ    ዕምነትን ብናፍቅ::
እንደዛሬው ሳይሆን
ባገሬማ ነበር    ገላጭ አባባል
ስም መርጦ ለውሻ    ድሮም ይሰጣል::
ባማረ ጥልፍ ሆነው    ግድግዳን ካስጌጡ
ለምሳሌ ያህል    እስቲ ይቺን አድምጡ::
"ሁለት ውሾች አሉኝ    የማሳድጋቸው
ሠርቶ ማደርና    ክፉን ችላ ናቸው::"
ይባል ነበር ድሮ
የየቅል ሆነ እንጂ    አምናና ዘንድሮ::

ዛሬማ:- እነሆ እናያለን    ግፉ ተባብሶ
ሠርተን እንዳናድር    አጠቃሎ ወርሶ
መቻቻል ቢባልም    መቻል አጎንብሶ
ባይገጥምም ከዛሬው    የድሮ ስሞች

ሌላ ስም አወጣሁ     ለራሴ ውሾች::
በጣም ምወዳቸው     ሁለት ውሾች አሉኝ
አንደኛውን "ዘርር!"     ብዬ እየጠራሁኝ
ለሁለተኛው ደግሞ
"ነጥል!"     የሚል ስም ሰጠሁኝ
ለእራሴ ቢሆንም
ግልፅነት አሰፈንሁ     እንዲህ እያረግሁኝ::

የእኔ ባላጋራ     ጋኞ ነው መንቻካ
እንደተጣበቀ     የማይለቅ ሾካካ
በየሄድኩበቱ
እየተከታተለ     ያለፈው ላይበቃ
ሲያበግነኝ ይኖራል     እኔን እያጠቃ::
ተንኮል ነው ሃሳቡ     ሲተኛም ሲነቃ
እያጠነጠነብኝ     ተቆጠርኩ እንደ ዕቃ::
እየተሳለቀብኝ     ሲከፋኝ ያሽካካል
በእኔ መሰቃየት     መንፈሱ ይረካል::

መታመቅ ቢበዛ     ቂም ቋጥሮ አንጀቴ
የተወጋ አይረሳም     ግን ቢታወቅ ጉዳቴ
ቀለል እንዲልልኝ     ብስጭት ጭንቀቴ
ዕምነትን ፈልጌ     ክዳትን ጠልቼ
እንስሳን መረጥኩኝ     ሰው ማመንን ትቼ::

"ዘርር" ውሻየማ
ትግል ሲገጥም ላየ     ያገባቡ ስልቱ
የሰው ቀልብ ይስባል     ንቃቱ ብርታቱ::

ዘቅዝቆ ሲያፈርጠው ጠላቱን ባናቱ
ስንቶች አደነቁት ባጣጣል ብልሃቱ::
ለእኔ እርሱ ብቻ ነው ከጭንቅ ገላጋየ
ሌላው እንኳን ቢቀር
ስሚቱን ሰጥቼ ለመካስ ቸኩየ
አውጥቼ:- አውርጄ ደርድሬ:- ቆልየ
ስም አወጣሁለት የእኔ "ዘርር" ብየ::
እነሆ! ደስ ሲለኝ!
አይተህ አትለፈኝ እያየ እንዳላየ
ከፊቴ አንብ እንጂ ሲታይ ፈገግታየ::

ጉዳቴን ያወቀው "ዘርር" አምበሳዬ
ልዩ ስጦታ አለው በሌሎች ያልታዬ::
ከሩቅ ጠረን ማሽተት ውሾች ይችላሉ
የሰውን ልጅ ከእንስሳ በልምድ ይለያሉ::
የክፉትን ጠረን! የከሃዲን ጠረን!
የባንዶችን ጠረን!
የግፈኛን ጠረን! ለይቶ ያወቀ
የኔው "ዘርር" ሆነ ከሌላው የላቀ::

በግቢያችን ይሁን ወይም ከዚያ ወጥቶ
ነፋሻማ ቦታ ከፍ ያለውን መርጦ
ከላይ ጉብ ይልና ግራ ቀኙን ቃኝቶ
ጠረን ተሸካሚው ነፋሱ በርትቶ
ከውሻየ አፍንጫ ሲዶለው አምጥቶ
ድንገት ፈትለክ ይላል እንደጦር አቅንቶ::
ክምችች ካሉት ሰዎች

ተንኮል ሸራቢውን ከሩቁ ለይቶ
መንጥቆ ያወጣዋል ስተት ብሎ ገብቶ::
ቂም የያዘብኝን:- የሚያሳድደኝን:-
ወልደ ሰይጣኑን
ያን ሕዝብ አስለቃሽ እጁ በደም የቀላውን
ማወቅ በመቻሉ አልፏል ፈተናውን::
የእኔን ባላጋራ ካጋጠመው ድንገት
አድብቶ በመዝለል ተጠምጥሞ ካንገት
ጠላት ይዘረራል እንዲያው ከመቅጽበት::

ዓይኑን ካይኑ ገጥሞ ከፊቱ አኩርፎ
በነጎድጓድ ድምፁ ውቃቤውን ገፎ
እንዳይሞት አድርጎ ቧጭሮ ነካክሶ
ሱሬውን ዘንጥሎ አውርዶ ከስክሶ
መሬቱን ፏግሮ አፈሩን አልብሶ
ዕብድ አስመስሎት ጠላቴን አቅምሶ
ወደ ቤት ይመጣል የልቡን አድርሶ::
ሊያናግረኝ አስቦ ጅንን ጉብልል ብሎ
አንዴ ይጮህና ፊቱን አኮሳትሮ
ጭራውን በመቁላት ሦስቴ እኔን ዙሮ
በእግሬ መሃል አልፎ መሬቱን ፏግሮ
ዓይን ዓይኔን እያየ ኮርቶ ተገትሮ
አጥቅቶ መምጣቱን ያበስራል ዘርዝሮ::

ንጹሕ ልብ ያለውን ባጠገቡ ቢያልፍም
በፍፁም አይነካም አይተናኮልም::
ሰብሰብ ካሉለትም ልጆችን ይወዳል

ከመሃል ቁጭ ብሎ　　ፎቶግራፍ ይነሳል
ኩዋሶች እያመጣ　　እንጫወት ይላል::

"በዘርር" ተነከስኩ　　ብለው ላማረሩ
የመካሰስ ጥቅሙ　　ቁስለት እያደሩ::
ይፈታ ካላችሁ　　እንዲሽር ችግሩ
በማስረጃ አቅርቡ　　በግልጽ ተናገሩ::
መርታትስ አትችሉም　　ሞልቶ ምስክሩ
ዘመድ አዝማድ ቢቀር　　አለ መቃብዕሩ::
ይልቅስ
ክህደት አትፈጽሙ!　　ዘረኛን አትሳሙ!
ጥላቻን አስቀሩ!　　ሕዝብን አታውድሙ!
ጉልበት ስላላችሁ　　ንብረት አትቀሙ::
ተራራ የሚያክል　　ስህተት እየሠሩ
ይቅርታን ቢጠይቅ　　እምን ላይ ነው ነውሩ?
የጠፋውን ሁሉ　　ይመን ከጅምሩ
እግዚአብሔር ያበቃው　　ይክሳል ከምሩ::
ንፁሕ ልብ መያዝ ነው　　እንዲቀል ችግሩ
አሣር እንዲወገድ
በኔም ሆነ ባንተ　　ወይም በሃገሩ
መቻቻል እንዲህ ነው
ከዚህ የተለየ　　ምንድነው ሚስጢሩ?

"ነጥል!"
ሌላኛው ውሻዬ　　ጠባዩ ይለያል
አካልን ባይጎዳም　　ጠላት ግን ያሳዳል::
የማሽተት ችሎታው　　ከሁሉም ይልቃል

ቀድሞ ያጣራና ለ"ዘርር" ይነግራል
"ዘርር" ተዘጋጅቶ ሊጎመር ያደባል::
በጣም ልበ-ሙሉ ከሆነ ግፊግኛው
ለሁለት ያጠኩታል እስከመጨረሻው::
የጠረጠረውን ዋናውን ግፊኛ
እየተከታተለ
እየጮኸ አይለቀውም ሲሮጥ ወንጀለኛ::
አባሮ አስደንግጦ
ያነን ተጠርጣሪ እየዞረው ሽርታ
መጮህ አያቆምም እኔ እስከምመጣ::
እኔም እንደደረስኩ ግብ ግቡ ሲግል
"ነጥል"! ተው! በቃ! ብዬ ሳላባብል
ምርኮኛን አይለቅም ሰማዩም ዝቅ ቢል::

ተፈጥሮ ሰጥታቸው የጠባይ ዓይነት
ብዙ ውሾች አሉ `ሚሠሩ ትንግርት::
እንደጠባያቸው ስልጠና ተሰጥተው
በርካታ ውሾችም ባለዲግሪ ናቸው::

ቦምብ ሆነ ፈንጅዎች ከመሬት ሚቀበር
ቅመማ ቅመምን አንዳች ንጥረ ነገር
ተደብቆ ሚያዝ ለሰው ማይነገር
አሽትቶ ያወጣል ምንም ሳይቸገር::

አንዳንድ ወንጀለኞች ስጋት ያለባቸው
ደንገጥገጥ እያሉ ፍርሃት ሲውጣቸው
ይፈጥራሉ ኢንዛይም ከውስጥ አካላቸው::

በአካላታቸው ውስጥ ሚሰርጸውን ቅመም
ለይቶ ያሸታል ምንም ሳይቀደም::
የፈራውን ይሁን ልቡ የተባውን
ወላዋዩን ሆነ ነገረ ሠሪውን
ለይቶ ያውቀዋል የሁሉን ጠባዩን::

ቀንደኛው ዘረኛ ሕዝብን ላስመረረ
ሕዝብን ለገደለ ጀግኖችን ላሠረ
ወያኔ መሳዩን ቀማኛ ግፈኛ
በውሻየ ፊት ሲያልፍ ሆኖ መንገደኛ
እየተከታተለ ቢሄድም እርቆ
በፍጥነቱ አጥፎት ጉርቦውን አንቆ
ምድር ቁና ሆና ጠላት በጥርስ ገብቶ
ዐይናችን ጉድ ያያል ትንቅንቁ ልቆ::

አየ ሰው! አየ ሰው! ከውሻ ሰው ያንሳል?
ጠላቱን ሳያውቀው ወዲያ ወዲህ ይላል::
አድብቶ አይዘርረው ወይ አያስፈራራው
ወይ ማሽተቱን አይችል መልካም ምግባር የለው
ሁሌ ጀሮ መጥባት መጠቆም ብቻ ነው::
ፈራ ተባ እያለ ከጠላቱ ጋራ ሲገባበዝ ውሎ
መወገን አቅቶት ዘመም ጠመም ብሎ
ከመንታ መንገድ ላይ ይቀራል ዋልሎ::

ሽክፍ ክውን ብሎ ንብረቱን አልያዘ
ሲቀሙት:- ሲገድሉት:- ሲሸጡት:- ሲለውጡት
እየተፋዘዘ

መርጦ ባስቀመጠው እየተጠመዘዘ
አበጀህ እያለ ግፈኛን እያገዘ
አንዴ ሳያልፍለት ኖረ እንደተከዘ::

ንግግር ሲያሰሙ አድምቆ ጭብጨባ
ወታደር አዝምቶ ሲጠና ድብደባ
ሰው እንዴት ይሠራል በራሱ ላይ ደባ::
አረ በማን አገር ሰው ከዉሻ ያንሳል?
ምግባር ሳያጠና ይክባል ይሰግዳል
ቃልን ሳይተረጉም ላይ ላዩን ይነጉዳል::
ያላንዳች ማመንታት ላምባገነን ሰግዶ
ዘፋኞች ሳይኖሩ አዳራሹ ባዶ
ዳንኪራ ያቀልጣል ድምፅን ብቻ ወዶ::
አረ እንዴት ተደርጎ?
የሰው ሁሉን በደል መሸከምን ይሻል?
ነፃ እንሁን ቀርታ መጣች እንቻቻል::
ትልቁ መቻቻል
አንድነት! ነፃነት! ብልፅግና! መተማመኛችን
መብት! ፍትሕ! እኩልነት! ክብረ-ሞገሳችን
ዘረኝነት ማጥፋት ሆኖ ምግባራችን
ይህን ከግብ ማድርስ
የሁዋሊት የማይሄድ ስርዬት ማስፈናችን
በጋራ ብንይዘው ጥቅሙ ለሁላችን::